# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

16



"ሸብርን ለመቋቋም አብዮታችን ወደ አጥቂነት ደረጃ መሸጋገር አለበት።"

ታኅሣሥ ፲፰ — ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.

## ርእሰ አንቀጽ ።

# ጠንካራ ወዳጆች ።

የአንድ አብዮት ወዳጅና ጠላቶች በዚያ ኅብረተሰብ ክልል ውስጥ ብቻ ተወስነው የሚታዩ አይደሉም ። ወዳጅና ጠላት እየተተነተነ የትግል ስልት በሚወጣበት ወቅት እንደጠላት ታይተው የሚጠበቁትና የሚመቱት በሀገር ውስጥ ያሉት በዝባዥ መደቦች ብቻ አይደሉም ። በየሀገሩ ያሉ በዝባገሮች በዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም አስተባባሪነት ባሕርን ፤ ወንዝን ፤ ተራራን ፤ ውቅያኖስን ፤ እያቆራረጡ እንደሸረሪት ድር የሚያደሩት የዓለም ጭቁን ሕዝቦችን ትግል አውተብትቦ ሊማፈን የሚፍጨረጨር ፀረ አብዮት አንድነት አላቸው ። ስለዚህ ነው በዛሬዩቱ ዓለም የማንኛውም ጭቁን ሕዝብ ትግል ፀረ ኢምፔሪያሊስት ይዘት የሚኖረው ። አንድ አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ ፤ ከኅብረተሰቡ ክልል ውጭ ጠላቶች እንዳሉት ካልተገነዘበ የጠላትን ኃይል ዝቅ አድርጐ መገመትና መዘናጋት ፤ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሲከላከል በሌላ አቅጣጫ የመመታት አደጋ ያጋጥመዋል ። ስለሆነም በዛሬዩቱ ዓለም የማንኛውም ሕዝብ አብዮት ጠላቶች በሚገመገሙበት ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙትን ጠላት ኃይሎች በተለይ ደግሞ ቀንደኛ አስተባባሪያቸውን ኢምፔሪያሊዝምን ከዋና ጠላቶቹ ቆጥሮ ሊታገለው ይገባል ። የኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝቦች አብዮት ፀረ ፊውዳል ብቻ ሳይሆን ፀረ ኢምፔሪያሊስት የሚሆነውም በዚሁ ምክንያት ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ የአብዮት ጠላትና ወዳጅ ተለይቶ ሲተነተን የማንም ሕዝብ አብዮት እንደዚሁ ከጠረፍ ባሻገር በዓለም አቀፍ ደረጃ ወዳጆች እንዳሉትም ሳይንሳዊ የሆነ ሀቅ ነው ። በአካባቢው አድኃሪው ኃይሎች ሊያጠፉት ከጠላት መደቦች ጋር ቢመሳጠሩ ፤ የአካባቢው ታጋይ ሕዝቦች ደግሞ የዚያኑ ያህል ለአብዮቱ ይቆረቆሩለታል ። ስለሆነም በዓለም አቀፍ ደረጃ ትግሉን ከዓለም አቀፍ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ጋር አስተባብሮ ሊቋቋማቸው ይሞክራል ። ይቋቋማቸዋል ። በዚሁ አንፃር ወዳጅና ጠላትን ሲተነትን በዓለም አቀፍ ደረጃ የአብዮቱን ወዳጆች ተገንዝቦ ከነሱ ጋር ኃይሉንና ትግሉን ለማስተባበር የማይሞክር ሕዝብ የራሱንም ትግል ወደፊት ለማራመድ የዓለም ጭቁን ሕዝቦችንም ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በቅጡ ለማገዝ ይሳነዋል ። በኃይለኛ ጠላቶቹ ላይ ማስተባበር የሚቻለውንም ኃይል መሰብሰብም ስለሚያቅተው ትግሉ ዘለቄታ አይኖረውም ።

የኢትዮጵያ አብዮት ወደፊት እየገፋ በሄደ ቍጥር በሀገሪቱ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ወዳጅና ጠላትን እየለየ መጥቷል ። በዚህ አንፃር ኢምፔሪያሊዝም የአብዮታችን ቀንደኛ ጠላት መሆኑ ብቻ ሳይሆን የጠቅላላው አድኃሪ ኃይሎች ትግል አጋርና አስተባባሪ እንደሆነ ጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዕለቱ በትግሉ ውስጥ ተገንዝቦታል ። ኢምፔሪያሊዝም በዛሬው ወቅት አብዮታችንን ለመቀልበስ ከቀኙ ክንፍ ንዑስ ከበርቴ አንስቶ እስከ መሳፍንቱ ድረስ ያሉትን



ቀልባሽ ኃይሎች በገንዘብ በመሣሪያ ፤ በፖለቲካና በምክር ይረዳቸዋል ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ድምፃቸውን ያስተጋባላቸዋል ። በሚነዛው ፕሮፓጋንዳ እንደአካባቢው እያየ መሳፍንቱን «የኮሙኒዝምን ግፊት ለመቋቋም የሚታገሉ ዲሞክራቶች» በማለት እየኳለ ያቀርባቸዋል ። ተራማጁን ዓለም ለማወናበድ ሲያሻው ደግሞ የለየላቸውን ፀረ ማርክሲስቶች « ኮሙኒዝምን ለመገንባት የሚታገሉ ሀቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶች » እያለ የአብዮት ካባ አስደርቦ በተራማጁ ዓለም ውስጥ በሰርጐ ገብነት እንዲደላደሉ ያደርጋል ። እነዚህ መሳፍንት «ዲሞክራቶችና» ፀረ ማርክሲስት «ማርክሲስቶች» በአንድ ግንባር ኃይላቸውን እንዲያስተባብሩም ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል ። ነገር ግን የአብዮታችን ጠላቶች እነዚህ ብቻ አይደሉም ። ጠንካራና አብዮታዊት የሆነች ኢትዮጵያን በአካባቢው የሚገኙ አድኃሪ መንግሥታት በፍራቻና በጥርጣሬ ቢመለከቷት ጨርሶ አያስገርምም ። ስለሆነም የአብዮታችን ጮራ በአካባቢው እንዳይፈነጥቅና የአካባቢው ጭቁን ሕዝቦች እነሱም በበኩላቸው ለሚያደርጉት አብዮታዊ ትግል ምሳሌና አጋር እንዳይሆን በመፍራት የአካባቢው አድኃሪ መንግሥታት ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ቀንደኛ ጠላቶች ጋር ፀረ አብዮት ትግላቸውን ያስተባብራሉ ።

ነገር ግን ከፍ ብለን እንዳልነው በዓለም አቀፍ ደረጃ አንድ ሕዝባዊ አብዮት ጠላትን በመቍጠር ብቻ አይወሰንም ። ወዳጆችም አሉት ። በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ እየተባበሩ አብዮቱን ለመቀልበስ የሚሯሯጡትን ፀረ አብዮት ኃይሎች ለመቋቋም አብዮታውያን በዓለም አቀፍ ደረጃም ኃይላቸውን ማስተባበር አለባቸው ። ለዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ የአንድ አብዮት ወዳጆች እነማን እንደሆኑ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል ።

በዚህ አንፃር ለብዙ ጊዜ የኢትዮጵያ አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉትን ወዳጆች ለይቶ ለማወቅ በነሱ ጐን ለመሰለፍና እነሱም ከጐኑ እንዲሰለፉ ለማድረግ አስቸጋሪ የሆነ ትግል አካሂዷል ። ፀረ አብዮት ኃይሎች በሀገር ውስጥ የአብዮቱን ኃይሎች ለመከፋፈል የጣሩትን ያህል በዓለም አቀፍ ደረጃም የኢትዮጵያን ጭቁኖች ትግል ብቸኛ ለማድረግ ፤ ከሀቀኛ ወዳጆቹ ነጥሎ ለማዳከምና ለመቀልበስ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ተጋድሎ ሲያደርጉ ቆይተዋል ። ነገር ግን የአብዮታችን ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ይዘት እየጠራ መሄዱ ፤ የሀገራችን መመሪያ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መሆኑ ተረጋግጦ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በይፋ መታወጁ ፤ ይህንንም በተግባር ለመተርጐም የኢትዮጵያ ጭቁኖች ከዕለት ዕለት በንቃት ፤ በድርጅትና በትጥቅ እየገፉ መሄዳቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠላቶቻችን ቁርጥ አድርገው ሚና እንደለዩ ያደረጋቸውን ያህል እንደዚሁም የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ፤ ሶሻሊስት አገሮችና ተራማጅ ኃይሎች ከመቸውም ይበልጥ ቁርጥ ባለ ሁኔታ ሚና ለይተው የአብዮታችን ጠንካራ አጋሮች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ።

የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባለፈው ሳምንት ኢትዮጵያን በጐበኙበት ወቅት « የኢትዮጵያ አብዮት በመላ ዓለም ጠንካራ ወዳጆች አሉት » ብለው የተናገሩት

ይህንኑ ሀቅ ለማረጋገጥ ነው ። አዎን ! የኢትዮጵያ አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ጠላቶች እንዳሉት ሁሉ እጅግ ጠንካራ የሆኑ ወዳጆችም አሉት ። በሀገር ውስጥ የአብዮት ወዳጅና ጠላት እየተለየ የአብዮትን ጠላት ለመደምሰስ የአብዮትን ወዳጅ ለማጠንከር ትግል እንደሚደረገው ሁሉ ዓለም አቀፍ ወዳጆችንና ጠላቶችን ለይቶ ተገቢ ርምጃ መውሰድም የአንድ አብዮት ድል መንሳት የሚጠይቀው ግዴታ ነው ።

የኢትዮጵያ አብዮት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠላቶቹን ያውቃቸዋል ። ጠንካራ ወዳጆቹንም በማወቅ ላይ ነው ። ነገር ግን ወዳጅን በማወቅ ብቻ አይወሰንም ። በጋራ ጠላቶችም ላይ በይበልጥ ኃይሉን በማስተባበር አብዮታችን ከሶሻሊስት አገሮች ፤ ከዓለም ጭቁን ሕዝቦችና ከፀረ ኢምፔሪያሊስት ታጋይ ኃይሎች ጐን ይሰለፋል ።

በዓለማችን ሰላም ፤ እኩልነት ፤ ነፃነት ፤ ዲሞክራሲና ሶሻሊዝም እንዲሰፍን የነዚህ ሁሉ ጠላት የሆነውን ኢምፔሪያሊዝምንና ቡችሎቹን መደምሰስ ያስፈልጋል ። ሀገራችን ለነዚህ አብዮታዊ ዓላማዎች በምትተናነቅበት በዛሬው ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠንካራ ወዳጆች እንዳሏት ማወቁ ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ትግል ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚሆን አይጠረጠርም ። በጋራ ጠላት ላይ በሚደረገው የጋራ ትግል የኢትዮጵያ ጭቁኖችም አብዮታቸውን ከግቡ አድርሰው በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም መቃብር ላይ ሕዝባዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ሲመሠርቱ የዓለም ሕዝቦች ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ጠንካራ አጋር እንደምትሆን አንጠራጠርም ።

**« የጭቁን ሕዝቦች ዓለም አቀፋዊ አንድነት የአብዮታዊ ድል ዋስትና ነው »**